**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
**ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**

**Addis Ababa University**
**Office of the President**

☏251-11-123 97 52
251-11-123 97 74
E-mail: poffice@aau.edu.et Website: www.aaa.edu.et

Addis Ababa Ethiopia
🖂 1176

# ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተሰጠ መግለጫ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፀረ-ፕላጃሪዝም (Anti-Plagiarism) ፖሊሲ አወጣ፡፡ ይህ ፖሊሲ ከየካቲት 22/2012 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን በፖሊሲው መሰረት ከዚህ በኋላ ማንኛውም መመረቂያ ጽሁፍ (Thesis/Dissertation) በአርከንድ (URKUND) ሶፍትዌር አማካይነት ተመርምሮ ከፕላጃሪዝም ነፃ መሆኑ ሳይረጋገጥ ለተማሪው ዲግሪ አይሰጥም፡፡

ፕላጃሪዝም ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ በራሳቸው ጥረት ራሳቸውን ችለው ኦርጅናል የሆነ ስራ ሰርተው እንዳያቀርቡ በማድረግ ዩኒቨርሲቲው ጥራትን ለማረጋገጥ በሚያደርገው ጥረት ላይ ትልቅ ጉዳት ሲያደርግ የቆየ ሕገወጥ ተግባር ነው፡፡ ቀደም ሲል የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ፕላጃሪዝም በመጠቀም የመመረቂያ ጽሁፉን በማዘጋጀት 2ኛ ዲግሪ ወስዶ ከነበረ ተማሪ ላይ ድርጊቱ በማስረጃ በመረጋገጡ በሴኔት ሕጉ መሰረት ዲግሪው እንዲነጠቅ አድርጓል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ይህ ችግር በመማር ማስተማሩና በምርምር ስራ ላይ በየጊዜው እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተፅእኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ የፀረ-ፕላጃሪዝም ፖሊሲ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ፖሊሲው ተግባራዊ ሲሆን ችግሩ ከሞላ ጎደል ይቃለላል የሚል እምነት አለ፡፡

ፕላጃሪዝም አንድ የምረቃ ፅሁፍ የሚያዘጋጅ ወይም የምርምር ስራ የሚሰራ ሰው ሌሎች ሰዎች የሰሩትን ስራ የራሱ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ የአካዳሚክና የምርምር ሕግጋትን በመጣስ የሚፈፅመው ሕገወጥ ተግባር ነው፡፡

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**
**ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**

https://www.urkund.com/the-urkund-system/

URKUND